# ሽረኛው በርጩማ!

## ከዓሣዬ

የሥንቱን ተሥፈኛ ፣ ጎሊናውን ሰቅሎ
ምርጫ በሚል ቧልቱ ፣ በዕጩነት መልምሎ፣
አልጠግብ ባዩን ሁሉ ፣ ልቦናውን ሰልቦ
እንደ ማር እንጎቻ ፣ የህልም እንጀራ አጥግቦ
ትርፍራፊ እንኳን ሣይሰጥ ፣ ከትከት ብሎ ሥቆ፣
ሽረኛው በርጩማ ፣ እያፌዘባቸው
እንደ ጥንግ አጉኖ ፣ ዘርሮ ጥሏቸው
ለመጪው አምሥት ዓመት ፣ እንገናኝ አላቸው።

አቤት ሃፍረት ማጣት፣ ጎሊና የሌሾች
እርምን የማያውቁ ፣ የግዑዝ ተምሣሌቶች
ለአሿፊው በርጩማ ፣ ለቱባ ወያኔዎች
ቅሬታ አሰሙ አሉ ፣ ለይግባኝ ሰሚዎች
ሥልጣን በልመና ፣ ከጅለው ቡከኖች ።

በታማኝ ሎሌነት ፣ ተመልምለው ገብተው
ለሁለገብ ትግሉ ፣ እንቅፋቱ ሆነው
ወህኒ የታጎረውን ፣ አናውቅህም ብለው
ከነ ሽብሬ ገዳይ ፣ እጅ ለጅ ተጨባብጠው
የሕዝቡን ጥያቄ ፣ ያገር ህልውናን ፣ ሳያነሱ ምለው
ግፉ እንዳይጋለጥ ፣ ሥነ ምግባር ፈርመው
ጽዋ አጋጭተው ጠጡ ፣ ለወያኔ ሰግደው ፣
ከዚያም ፣
ሚዛን ማያነሱ ፣ መሆናቸውን አይቶ
የቋመጡላትን ፣ በርጩማዋን ነሥቶ
እንደ ዶሮ ላባ ፣ በቅሌት አንሣፎ
ሽረኛው ወያኔ ፣ ተፋቸው አቀርሽቶ ።

ጆሮ ያለህ ሥማ ፣ ልብ ያለህ አሥተውል
እራሱን ላሥቀደመ ፣ ኪሱ እንዳይጎድል ፣
አገርንም ከድቶ ፣
ሕዝብንም አጋልጦ ፣ ከጠላት አዳሪውን
መርገምትን አግልለህ ፣ ውግዝ ከመ አሪዎሱን ፣
እንዳይከፋፍልህ ፣ ውሥጥህን አጥርተህ
ዕርመ በላ ባንዳን ፣ በጽኑ ተዋግተህ
አገርህን ለማዳን ፣ ከታጋይ ወግነህ
ግዜ የለህምና ፣ ተነሥ ተደራጅተህ
በቀጣዩ ምርጫ፣ መዘናጋት ትተህ ።

07/16/2010

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.